የሰ/መ/ቁ. 73549

ሰኔ 22 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፌሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** የዲላ ዩንቨርስቲ - ነገረፈጅ ተዘራ ገዳሙ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1ኛ. አቶ የትናየት ጣፋ - የቀረበ የለም

2ኛ. አቶ ዳግም ጫላ - ቀረቡ

3ኛ. አቶ ነጌሳ ጥላሁን - የቀረበ የለም

መዝገቡ ያደረው ለውሳኔ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ተጠሪዎች በዲላ ዩንቨርስቲ በተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ክፍል ከTA II ወደ GA II የደረጃ እድገት እንዲሰጠን በተለያዩ የስራ ክፍሎች የተወሰነ ሆኖ ያልተፈጸመ ስለመሆኑ በማመላከት የደረጃ እድገቱ እንዲሰጣቸው እና ክፍያውም ከተወሰነላቸው ቀን ጀምሮ እንዲከፈለን በማለት የቀረበውን ክስ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የደቡብ ክልል የጌድኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር በመስማት የደረጃ እድገቱም እንዲሰጣቸው እና ክፍያውም እንዲፈጸምላቸው ውሳኔ ሰጥቷል፣ ይሄው ውሳኔ በክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤትም በመጽናቱ አመልካች የተፈጸመው መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ የቀረበ ነው፡

አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያላቸውን ነጥቦች ያነሳ ሲሆን ፍሬ ሃሳቡ፡- ተጠሪዎች በክሳቸው የተመለከተውን የደረጃ እድገት እንዲያገኙ በትምህርት ክፍላቸው አማካኝነት ለፋኩልቲው ቀርቦ እና ፋኩልቲውም ለተቋሙ ኘሬዚዳንት አስተላልፎታል፣ ሆኖም ይሄ የደረጃ ዕድገት ሊተገበር የሚችለው የፌ/ሲቪል ሰርቪስ ውክልና ያለው የፌ/ትምህርት ሚንስቴር የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ሲያጸድቀው በመሆኑ እና ይሄንን በማጽደቅ ያልመለሰ በመሆኑ የምፈጽመው የእድገት ጥያቄ የሌለ በመሆኑ በኋላ ላይ በትምህርት ሚንስቴር በተላለፈው ሰርኩላር መሰረት ዩንቨርስቲው የሚያያቸው የእድገት ጥያቄዎች ሊታዩ የሚችሉ ሁነው አሁን በፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ግን ከመመሪያ ውጭ እንድንሰራ የሚያደርግ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ቀደም ሲል በዩንቨርስቲው የተጻፈው ደብዳቤም ቢሆን ተጠሪዎች ወደ ደረጃ GA-I እንዲያድጉ እንጂ ወደ ደረጃ GA-II ባለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጠት ውሳኔ አግባብነት የሌለው በመሆኑ እንድታረምልን የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል የስር ፍርድ ቤቶች ይሄንን ጉዳይ አይተው ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን ያላቸው መሆን አለመሆንን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.9 አንጻር ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት በመታዘዙ መልሳቸውን ሰጥተውበታል፡፡ የተሰጠውም የመልስ ፍሬ ሃሳብ፡- ለፍርድ ቤቱ ያቀረብነው ክስ በመካከላችን ያለውን ውል ይፈጸም እንጂ ያቀረብነው የደረጃ እድገት ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ይሄንን የፍታብሔር ክስ መመልከት ይችላል፡ አስፈላጊውን ሰነዶች ፍርድ ቤቱ ከስራ ክፍላችን በማስመጣት መመልከት የሚችል በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶችም የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ባቀረበው የመልስ መልስ አመልካች የመንግስት መስሪያ ቤት እንደመሆኑ መጠን የሚተዳደረው በፌ/የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 መሰረት በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ይሄንን ክስ የማስተናገድ ስልጣን የላቸውም በሚል ቅሬታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

በግራቀኙ መካከል የተደረገው የክርክር ሂደት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ይሄንን ጉዳይ መደበኛ ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ክሱን ተመልክተው ውሳኔ ሊሰጡበት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በመመልከት ለተያዘው ጉዳይ እልባት መስጠት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች የደረጃ እድገት እንዲያገኙ በዩንቨርሲቲው የተለያዩ የስራ ክፍሎች የውሳኔ ሃሳብ የተጻጻፉ ስለመሆኑ፣ ሁኖም ግን በስተመጨረሻ ለትምህርት ሚንስቴር የተጻፈ የውሳኔ ሃሳብ ስለመኖሩ እና የትምህርት ሚንስተር የቀረበለትን የደረጃ እድገት በማጽደቅ ያልመለሰ ስለመሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፣ ሆኖም ግን የክልሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠየቀውን የደረጃ እድገት ጥያቄ የትምህርት ሚንስተር በማጽደቅ አልመለሰልኝም በማለት እጁን አጣጣፎ መቀመጥ የለበትም በማለት የደረጃ እድገቱም ሆነ ክፍያው እንዲፈጸምላቸው ውሳኔ የሰጠ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡

ከዚህ ሁሉ ክርክር እና በታች ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር መገንዘብ የሚቻለው አከራካሪው ጉዳይ የደረጃ እድገት የሚሰጥበትን አግባብ የሚመለከት እንጂ ተጠሪዎች እንደሚሉት የውል ግንኙነትን መሰረት ያደረገ  የፍትሐብሔር ክርክር አለመሆኑን ነው፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ ይሄንን የደረጃ እድገት ጥያቄ ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ተቀብለው ማስተናገድ የሚችሉ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በመመልከት ለተያዘው ጉዳይ እልባት መስጠት ተገቢነት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ጉዳዩን ስንመለከት ተጠሪዎች የዲላ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ክፍል ውስጥ የሚሰሩ ስለመሆኑ እና መስሪያ ቤቱም የመንግስት መስሪያ ቤት ስለመሆኑ ግራቀኙን አላከራከረም፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው የህግ ማዕቀፍ እንዳግባብነቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን መመልከት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ የህግ ማዕቀፎች አጠቃላይ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ የፌዴራል የመንግስት ተቋም ባጠቃላይ እና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን በተለይ የራሱ የሆነ የእድገት አሰጣጥ፣ የቅሬታ አፈታት እና አጠቃላይ አስተዳደራዊ ስራዎችን የሚያከናውኑበትን አግባብ ያስቀመጡ ስለመሆኑ መመልከት ይቻላል፡፡

ይሄ ከሆነ ደግሞ የተጠሪዎች የደረጃ እድገት ክርክር በእነዚሁ አዋጆች በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ታይቶ እልባት ከሚያገኝ በስተቀር በቀጥታ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት እና ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በቀጥታ አይተው ውሳኔ የሚሰጡበት አግባብ አይኖርም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩ ሲቀርብላቸው ስልጣን እንደሌላቸው በመገንዘብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 9፣231/1/ለ/ ፣244/2/ሀ/ መሰረት መመለስ ሲገባቸው ክሱን በመቀበልና በማከራከር ውሳኔ መስጠታቸው አግባብነት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ባጠቃላይ የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ባቀረቡት የደረጃ እድገት ጥያቄ ላይ ስልጣን ሳይኖራቸው የሰጡት ውሳኔ አግባብነት የሌለውና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የደቡብ ክልል የጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 53540 በቀን 06-12-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት እና የክልሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ.ቁ 05259 በቀን 08-09-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የመደበኛ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን የደረጃ እድገት ጥያቄ በመመልከት ውሳኔ ለመስጠት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ብለናል፡፡ ይህ ማለት ግን ተጠሪዎች መብታቸውን በህጉ በተቀመጠው ስርዓት መሰረት መብታቸውን ከመጠየቅ ይሄ ውሳኔ አያግዳቸውም፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር በግራቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ